መልእክት ስድስት

**ለእግዚአብሔር ዓላማ**

**በእግዚአብሔር ለመለወጥ እግዚአብሔርን ማትረፍ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኢዮብ 42፡1-6፤ 2 ቆሮ. 3፡8-9፤ 4፡10-12፣ 16-18፤ 5፡18-20

**I. በኢዮብ ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ በሰማያዊው ራእይ እና በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እውነታ የሚኖር ሰው ይሆን ዘንድ ነበር፦**

ሀ. የኢዮብ ልምምድ እግዚአብሔር እርሱን በእግዚአብሔር በራሱ መልሶ መገንባት የሚችልበት መንገድ ያገኝ ዘንድ እና እግዚአብሔርን በጥልቀት ወደ መፈለግ ውስጥ እግዚአብሔር እርሱን ያስገባው ዘንድ፣ በእግዚአብሔር በረከቶች ምትክ እና ኢዮብ በፍጹምነቱና በግብረገባዊነቱ ባገኛቸው ስኬቶቹ ምትክ እግዚአብሔርን ያተርፍ ዘንድ፣ ኢዮብን ለማፈራረስ የረካውን ኢዮብ የመጨረስ እና የመግፈፍ፣ በመለኮታዊ ኢኮኖሚው በእግዚአብሔር የተወሰደ እርምጃ ነበር—ፊልጵ. 3፡10-14፤ 1 ቆሮ. 2፡9፤ 8፡3፤ ዘጸ. 20፡6፤ 1 ዜና 16፡10-11፤ 22፡19፤ 2 ዜና 12፡14፤ 26፡3-5፤ 34፡1-3፤ መዝ. 24፡6፤ 27፡4፣ 8፤ 105፡4፤ 119፡2፣ 10፤ ዕብ. 11፡6።

ለ. ለእግዚአብሔር ግድ የማይሰኝ ሰው ብዙ ነገሮችን ሊያተርፍ እና እየበለፀገ ያለ ሊመስል ይችላል (መዝ. 73፡1-15)፤ ሆኖም ግን፣ ለእግዚአብሔር ግድ የሚሰኝ ሰው በእግዚአብሔር ይገደባል፣ እንዲያውም ከብዙ ነገሮችም ሳይቀር በእግዚአብሔር ይገፈፋል፤ እግዚአብሔር በፈላጊዎቹ ላይ ያለው ውጥን በእርሱ ሁሉን ነገር እንዲያገኙ እና እርሱን ራሱን ከሚደሰቱበት ፍጹም ድሰታቸው እንዳይዘናጉ ነው (ቁ. 16-28)።

ሐ. ቅዱስ ሕዝቡን በማደቡ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ከሁሉ ነገር ባዶ ይሆኑ እና እግዚአብሔርን ብቻ እንደትርፋቸው ይቀበሉ ዘንድ ነው (ፊልጵ. 3፡8፤ ተዛ. መዝ 73፡25-26)፤ የእግዚአብሔር የልቡ መሻት እርሱን ለማንነታችን እንደ ሕይወት፣ እንደ የሕይወት አቅርቦት እና እንደ ሁሉ ነገር በሙላት እናተርፈው ዘንድ ነው (ሮሜ 8፡10፣ 6፣ 11፤ ተዛ. ቆላ 1፡17፣18)።

መ. ከመለኮታዊው እደላው ጋር በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እውነታ ለመኖር፣ ማንነታችን በክርስቶስ እንደገና እንዲቀናበር ወደ ውስጠ-መሠረታዊው ቅንብራችን ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ይገነባ ዘንድ ያስፈልገናል፦

1. በጳውሎስ መልእክቶች እንደተገለጠው፣ እግዚአብሔር እኛን የማደቡ ዓላማ እግዚአብሔርን ጨምረን ጨምረን እናተርፈው ዘንድ ከሁሉ ነገር ይገፍፈን እና እኛን ይጨርሰን ዘንድ ነው—2 ቆሮ. 4፡16-18።
2. የቤተ ክርስቲያን መገንባት ክርስቶስ ቤቱን በልባችን ውስጥ በመሥራቱ፣ ማለትም፣ ራሱን ወደ እኛ ውስጥ በመገንባቱ፣ ውስጠ-መሠረታዊ ቅንብራችንን፣ ልባችንን፣ ቤቱ ማድረግ ነው—ኤፌ. 3፡16-21።

ሠ. በክርስቶስ እግዚአብሔር ሰው ውስጥ ተቀናበረ፣ ሰው እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናበረ፣ በተጨማሪም እግዚአብሔር እና ሰው አንድ አካል ለመሆን ተዋሐዱ፤ ይህ የሚያመለክተው በኢኮኖሚው ያለው የእግዚአብሔር ውጥን፣ በሕይወት እና በባሕሪ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ ራሱን ሰው ማድረግ እንደሆነ ነው—2 ሳሙ. 7፡12-14፤ ሮሜ 1፡3-4፤ ማቴ. 22፡41-45፤ ዮሐ. 14፡6፤ 10፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ዮሐ. 6፡63፤ 2 ቆሮ. 3፡6፤ 1 ዮሐ. 5፡16።

**II. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ብዙዎች የተካተቱበትን አምላክ-ሰው ያገኝ ዘንድ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ እና ሰው በእግዚአብሔር ውስጥ ለመገንባቱ፣ በመንፈስ በልውጠት በኩል ሰው አምላክ መሆን ይችል ዘንድ በተሠግዎ በኩል እግዚአብሔር *ሥጋ* በመልበስ ሰው መሆኑ ነው፦**

ሀ. ዘላለማዊው እና ሦስታንዱ አምላክ ሰው በመሆኑ እጅግ እጹብ-ድንቅ፣ የላቁ፣ ምሥጢራዊ እና ሁሉን-ያካተቱት ልውጠቶቹ ለዘላለማዊው ኢኮኖሚው መፈጸም የእግዚአብሔር በሰው ውስጥ መንቀሳቀስ ናቸው—ሚክ. 5፡2፤ ዮሐ. 1፡14፣ 29፤ 3፡14፤ 12፡24፤ ሐዋ. 13፡33፤ 1 ጴጥ. 1፡3፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሐዋ. 2፡36፤ 5፡31፤ ዕብ. 4፡14፤ 9፡15፤ 7፡22፤ 8፡2፦

1. እነዚህ ልውጠቶች አምላክ-ሰው በመሆኑ፣ እንደ ዋናው ሞዴል ለብዙ አምላክ-ሰዎች ርቢ መለኮትን ወደ ስብዕና ውስጥ በማምጣቱ እና መለኮትን ከስብዕና ጋር በማዋሐዱ ሦስታንዱ አምላክ ያለፈባቸው ሂደቶች ናቸው፤ እርሱ እግዚአብሔርን ወደ ሰው በማምጣት እና እግዚአብሔርን ሊገናኙት የሚችሉ፣ የሚነካ፣ የሚቀበሉት፣ የሚለማመዱት፣ የሚገቡበት እና የሚደሰቱት በማድረግ የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ ሆነ—ዮሐ. 1፡14፤ ቆላ. 2፡9፤ ሮሜ 8፡28-29።
2. እግዚአብሔር በሆሴዕ 11፡4 ስለነዚህ ልውጠቶች "በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው" በማለት ይናገራል፤ *በሰው ገመድ፣ በፍቅርም* የሚለው ሃረግ እግዚአብሔር በመለኮትነት ደረጃ ሳይሆን በስብዕና ደረጃ በመለኮታዊ

ፍቅሩ እኛን እንደሚወደን ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ፍቅር መለኮታዊ ነው፣ ነገር ግን እኛን በሰው ገመድ፣ ማለትም በክርስቶስ ስብዕና በኩል ይደርሰናል፡-

ሀ. እግዚአብሔር እኛን የሚስብበት ገመዶቹ (ልውጠቶቹ፣ ሂደቶቹ) የክርስቶስን ተሠግዎ፣ የስብዕና ኑሮ፣ መሰቀል፣ ትንሣኤው እና ዕርገት ያካትታሉ፤ በእነዚህ በስብዕናው ባሉ የክርስቶስ ደረጃዎች ሁሉ ነው የእግዚአብሔር ፍቅር በማዳኑ እኛን የሚደርሰን—ኤር. 31፡3፤ ዮሐ. 3፡14፣ 16፤ 6፡44፤ 12፡32፤ ሮሜ 5፡5፣ 8፤ 1 ዮሐ. 4፡8-10፣ 16፣ 19።

ለ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር፣ የማይለወጠው፣ አሸንፎ-የሚገዛው ፍቅር፣ ከክርስቶስ ውጭ ከእኛ ጋር በተገናኘ ሊያሸንፍ አይችልም፤ የእግዚአብሔር የማይለወጠው ፍቅር አሸናፊ የሆነው በክርስቶስ ውስጥ፣ ከክርስቶስ ጋር፣ በክርስቶስ እና ለክርስቶስ ስለሆነ ነው።

ሐ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር ሁልጊዜም አሸናፊ ነው፤ በስተመጨረሻ፣ ምንም እንኳን ውድቀቶች እና ስህተቶች ቢኖሩንም፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ድሉን ያገኛል—ሮሜ 8፡35-39።

ለ. ሦስት ክፍል ያለው ሰው ልውጠት ሰውን መለኮት የማድረግ፣ በሂደት ባለፈውና በተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ሰውን የማቀናበር የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ነው፤ እግዚአብሔር ለኢዮብ በመገለጡ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ዓላማ በእግዚአብሔር ለመለወጥ እግዚአብሔርን ለማትረፍ እግዚአብሔርን አየ—ኢዮብ 38፡1-3፤ 42፡1-6፤ 2 ቆሮ. 3፡16-18፤ ዕብ. 12፡1-2፡-

1. እግዚአብሔርን ማየት የማንነታችንን ወደ እግዚአብሔር መልክ መለወጥ ያመጣል፤ በመሆኑም፣ እርሱን በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለ የተጠናቀቀው መንፈስ አብዝተን ባየን መጠን፣ መላው ማንነታችን አዲስ ይሆን ዘንድ አሮጌው ንጥረ-ነገራችን እንዲወገድ የእርሱን ንጥረ-ነገሮች ሁሉ እንደ መለኮታዊ ንጥረ-ነገር አብዝተን እንቀበላለን፤ የክርስቲያን ሕይወታችን በውጭ የመለወጥ ጉዳይ ሳይሆን ከውስጥ የመለወጣችን ጉዳይ ነው—2 ቆሮ. 3፡18፤ መዝ. 27፡4፤ ገላ. 6፡15-16።

2. በመጋረጃ በማይከደን ፊት ጌታን ትኩር ብለን ማየት እና ማንጸባረቅ እንችል ዘንድ ልባችንን ወደ ጌታ በማዞር በዕለት ተዕለት የልውጠት ሂደት ውስጥ መቆየት እንችላለን፤ በመጋረጃ ያልተከደነ ፊት ወደ ጌታ የሚዞር ልብ ነው—2 ቆሮ. 3፡16፣18፡-

   ሀ. ልባችንን ወደ ጌታ ማዞር ጌታን መውደድ ነው፤ ጌታን አብልጠን በወደድን መጠን፣ ልባችን አብልጦ ለጌታ ይከፈታል፣ እርሱም ከመንፈሳችን ወደ የልባችን ክፍሎች ሁሉ ውስጥ ለመሰራጨት መንገድ ያገኛል።

   ለ. ልባችንን ወደ ጌታ ማዞር፣ ልባችንን ለጌታ መክፈት በሕይወት ለማደጋችን ቁልፉ ነው፤ “ኦ ጌታ፣ እወድሃለሁ፤ አንተን ደስ ማሰኘት እፈልጋለሁ” ብለን ለጌታ በቀላሉ በመንገር ልባችንን ለጌታ መክፈት እንችላለን።

   ሐ. በሁኔታዎቻችን ሁሉ ጌታን ዕለት ዕለት ትኩር ብለን ስንመለከተው (መዝ. 27፡4) የጌታን ክብር እናንጸባርቃለን፣ በተጨማሪም ከክብር ወደ ክብር ወደ እርሱ መልክ እንለወጣለን።

   መ. ብዙ ክርስቲያኖች ደስተኞች ያልሆኑት በውስጣቸው ያለው መንፈስ ደስተኛ ስላልሆነ ነው (ኤፌ. 4፡30፤ ተዛ. መዝ. 16፡11፤ 43፡4፤ ሐዋ. 3፡19-20፤ ዘጸ. 33፡11፣ 14-17፤ ዕብ. 1፡9፤ ኤር. 15፡16፤ ዮሐ. 15፡9-11፤ 1 ዮሐ. 1፡3-4፤ 2 ዮሐ. 12፤ ፊልጵ. 4፡4)፤ የጌታ መንፈስ ከመንፈሳችን ወደ ልባችን ውስጥ እንዲሰራጭ ልባችንን ወደ ጌታ ካላዞርን፣ እንደተገደብን እና እንደተደበትን ይሰማናል።

   ሠ. የጌታ መንፈስ ባለበት፣ በዚያ አርነት አለ (2 ቆሮ. 3፡17)፤ አንድ ሰው አንድን ስብሰባ ይደብታል ካለ፣ እርሱ ራሱ በውስጡ እንደተደበተ መገንዘብ አለብን፤ ነገር ግን ልባችንን ወደ ጌታ ስናዞር፣ መንፈስን እንደ ነጻነታችን እንደሰተዋለን።

   ረ. አርነት የሚያወጣው መንፈስ አንድ ጊዜ ወደ ልባችን ክፍሎች ሁሉ ለመሰራጨት መንገድ ካገኘ እንለቀቃለን፣ ከፍ እንላለን እና ነጻ እንሆናለን፤ የእግዚአብሔር መገኘት እና የእግዚአብሔር መገለጥ የሆነው ይህ አርነት ክብር ነው፤ ወደ እርሱ መልክ እየተለወጥን ስለሆነ ክቡር እና ምስጉን እንደሆንን ይሰማናል—ቁ. 18፤ ዘፍ. 1፡26።

ሐ. ልውጠት ከአንድ መልክ፣ ከአሮጌው ሰው መልክ፣ ወደ ሌላ መልክ፣ ወደ አዲሱ ሰው መልክ ያሻግረናል፤ ጌታ ይህን የልውጠት ሥራ የሚያከናውነው በክርስቶስ ሞት መግደል አማካኝነት ነው—2 ቆሮ. 4፡10-12፣ 16-18፡-

1. በ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡10 ጳውሎስ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን ይላል፤ *መሞት* ማለት መግደል ማለት ነው፤ የክርስቶስ ሞት ይገድለናል—1 ቆሮ. 15፡31፣ 36፤ ዮሐ. 12፡24-26፤ 2 ቆሮ. 1፡8-9።

2. የክርስቶስ ሞት በተቀመመው መንፈስ ውስጥ ነው፤ መንፈስ የክርስቶስ ሞት እና የሞቱ ፍቱንነት መተግበር ነው—ዘጸ. 30፡22-25፤ ሮሜ 8፡13።

3. የክርስቲያን ሕይወት ሁልጊዜ በተቀመመው መንፈስ መግደል ሥር የሆነ ሕይወት ነው፤ ይህ የየዕለት መግደል የሚካሄደው እንደሚገድል መሣሪያ ከሚሠራው ከባቢው ሁኔታችን ጋር በውስጣችን በሚያድረው መንፈስ ነው።
4. በእግዚአብሔር መለኮታዊ እና ሉዓላዊ አዘገጃጀት፣ በክርስቶስ ሞት መግደል በኩል ነገር ሁሉ ለበጎ፣ ለልውጠታችን ይሠራልናል፤ በሮሜ 8፡28 "በጎ"ው ከሰዎች፣ ከጉዳዮች ወይም ከነገሮች ጋር አይገናኝም፤ አንድ ብቻ በጎ ነው—እግዚአብሔር—ሉቃ 18፡19፡-
   ሀ. በበጎ (መዝ. 68፡19)፣ በራሱ በሦስታንዱ አምላክ (ተዛ. ዘፍ. 45፡5፤ 50፡20) መሞላት እንችል ዘንድ ከእኛ ጋር የተገኛኙ ሰዎች ሁሉ፣ ጉዳዮች ሁሉ እና ነገሮች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በጎ እንዲሠራልን መንገዶች ናቸው።
   ለ. እንድንለወጥ እና የእግዚአብሔርን በኩር ልጅ መልክ እንድንመስል በውስጣችን ካለው ሥራ ጋር ይገጣጠም ዘንድ ከእኛ ጋር የሚገናኙ ሰዎች እና ሁኔታዎች በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተዘጋጁ ናቸው—ተዛ. ማቴ. 10፡29-31።

መ. የመንፈስ ቅዱስን ቅጣት ስንለማመድ ሳለ ልውጠት በውስጣችን ይከናወናል—ሮሜ 8፡2፣ 28-29፤ ዕብ. 12፡5-14፡-
1. በውስጣችን ያለው የመንፈስ ሥራ ለእኛ አዲስን ማንነት ማቀናበር ነው፣ ነገር ግን ከውጭ ያለው የመንፈስ ሥራ በከባቢ ሁኔታችን አማካኝነት የፍጥረታዊውን ማንነታችን እያንዳንዱን ገጽታ ማፈራረስ ነው—ተዛ. ኤር. 48፡11።
2. በውስጣችን ከሚሠራው መንፈስ ጋር መተባበር እና እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ከባቢ ሁኔታ መቀበል አለብን—ፊልጵ. 4፡12፤ ኤፌ. 3፡1፤ 4፡1፤ 6፡20፤ 1 ቆሮ. 7፡24።

## III. አገልግሎት የመገለጥ እና የመከራ ውጤት ነው—የምናየው ነገር በመከራ በኩል ወደ ውስጣችን ይገነባል፤ ስለዚህ፣ የምናገለግለው የሆንነውን ነገር ነው፡-

ሀ. ምንም እንኳን አገልጋዮቹ ብዙ ቢሆኑም አንድ አገልግሎት—ለእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ መፈጸም የሆነው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት—ብቻ አላቸው፤ ከክርስቶስ ጋር አብረን መሥራታችን ይህን ልዩና ብቸኛ አገልግሎት፣ ለአካሉ መገንባት ክርስቶስን ወደ ሰዎች ውስጥ ማገልገልን ማከናወን ነው—ሐዋ. 1፡17፤ ኤፌ. 4፡11-12፤ 1 ጢሞ. 1፡12፤ 2 ቆሮ. 4፡1፤ 6፡1።

ለ. እንደ አንድ ጥቅል፣ አካሉ አንድ፣ ልዩና ብቸኛ የሆነ ብዙዎችን ያካተተ አገልግሎት አለው፣ ነገር ግን ይህ አገልግሎት የክርስቶስ አካል አገልግሎት ስለሆነ እና አካሉ ብዙ ብልቶች ስላሉት፣ ብልቶች ሁሉ ይህን ልዩና ብቸኛ አገልግሎት ለማከናወን የራሳቸው አገልግሎት አላቸው—ሐዋ. 20፡24፤ 21፡19፤ 2 ጢሞ. 4፡5፤ ቆላ. 4፡17።

ሐ. አገልግሎቱ የተለማመድነውን ክርስቶስ ለሌሎች ለማገልገል ነው፣ ይህ አገልግሎት ደግሞ የተቀናበረው፣ የፈራው እና የተሠራው በመከራዎች፣ በሚጨርሱ ግፊቶች እና በሚገድለው የመስቀሉ ሥራ ውስጥ ባተረፍነው የክርስቶስ ብልጥግናዎች ልምምድ ነው—ሐዋ. 9፡15-16፤ ቆላ. 1፡24፤ ፊልጵ. 3፡10፤ 1 ጢሞ. 4፡6፤ 2 ቆሮ. 1፡4-6፤ 8-9፤ 12፤ 3፡3፤ 6፡-
1. የመንፈስ አገልግሎት ሕይወት እንደሚሰጥ መንፈስ ክርስቶስን በማገልገላችን ወደ መለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ ለመድረሳችን ነው—ቁ. 8-9፣ 6፣ 3፤ ራእ. 22፡17።
2. የጽድቅ አገልግሎት ክርስቶስን እንደ ውጫዊ ጽድቃችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እውነተኛ ለሆነው የክርስቶስ መገለጥ እንደ ልምምዳዊ እና ከውስጥ ወደ ውጭ እንደምንኖረው ጽድቃችን እርሱን ለሌሎች በማገልገላችን ወደ አምላክ-ሰው ኑሮ ውስጥ ለመግባታችን ነው—ሮሜ 5፡17፤ ፊልጵ. 3፡9፤ ራእ. 19፡8።
3. የማስታረቅ አገልግሎት የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈሳቸው ውስጥ ያሉ ሰዎች ይሆኑ ዘንድ ቅድስተ ቅዱሳን ወደሆነው መንፈሳቸው ውስጥ እነርሱን በማምጣት ክርስቶስን ለሰዎች እንደ ማስታረቅ ቃል በማገልገል ሰዎችን በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ (በሰማያዊ የእረኝነት አገልግሎቱ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን) ነው—2 ቆሮ. 5፡18-20፤ ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 5፡2-4፤ 2፡25፤ ራእ. 1፡12-13፤ ዕብ. 10፡19፣ 22፤ 1 ቆሮ. 2፡15።
4. በሦስቱ ገጽታዎቹ እንዲህ ወዳለ ድንቅ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በመግባታችን፣ ጌታ አብያተ-ክርስቲያናትን ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ ለማስገባት መንገድ ያገኛል።

መ. መከራ ከክርስቶስ ብልጥግናዎች ሁሉ ጋር የጸጋ ጣፋጭ ጉብኝት እና ተሠግዎ ነው፤ ጸጋ በዋነኛነት የሚጎበኘን በመከራ መልክ ነው—2 ቆሮ. 12፡7-10፡-
1. በመከራዎች በኩል በፍጥረታዊው ማንነታችን ላይ የክርስቶስ መስቀል የመግደሉ ውጤት በእኛ ላይ የሚተገበረው በመንፈስ ቅዱስ ነው፣ ይህም የትንሣኤው አምላክ ራሱን ወደ ውስጣችን እንዲጨምር መንገድ ይሰጣል—1፡8-9፤ 4፡16-18።

2. መከራ የተቀባይነትን ባሕርይ—በመከራ እና በፈተና ውስጥ በመጽናት እና መከራን እና ጽናትን በመለማመድ ተቀባይነት ያለው ባሕርይ—የሚያመጣውን ጽናትን (ትዕግሥትን) ያፈራል—ሮሜ 5፡3-4።

ሠ. በመከራዎቻችን ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጥ ዘንድ እግዚአብሔር በውስጣችን እንደሚያነሳሳን ኃይል፣ በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ራሱን እንደ ፍቅር አፈሰሰ፤ ስለዚህ፣ ምንም አይነት ፈተና ውስጥ ስንጸና ክርስቶስ ለመጉላቱ እርሱን እንኖራለን እንጂ አናፍርም—ቁ. 5፤ 8፡31-39፤ 2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ፊልጵ. 1፡19-21።

*© 2020 Living Stream Ministry*